# ያልታተመው ቃለ ምልልስ

# በዚያች ዕለት- ከዶክተር ብርሀኑ ጋር

**ደረጀ ሀብተወልድ- ከአምስተርዳም**

በአራራይ ቅላፄ  የታጀለውና ፤ ***"አድነነ ከመዐቱ ሰውረነ"*** የሚለው ፤የቀጨኔ መድሀኒዓለሙ ካህን ፤የሚያስገመግምና የሚያባባ  ድምፅ ፤እንደውድቅት ሌሊት የሚደብተውን  የማለዳ ፀጥታ ሰንጥቆ  ጆሮዬ ላይ ሲያንቃጭል ነው ከዕንቅልፌ የነቃሁት።

የአዲስ አበባ ሰማይ በጥቁር ጭጋግ ተሞልቷል።ለወትሮው ፤ ገና ከማለዳው አንስቶ ወዲያ ወዲህ የሚርመሰመሱት ታክሲዎች ፤ዛሬ ፤ ልክ -ዝግ ሱባዔ እንደገባ ባህታዊ ፤እስከረፋዱም ድረስ ሊታዩ አልቻሉም።የትራንስፖርት እንቅስቃሴው የቆመበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ ጋር ተያይዞ፤ የእግረኛውም ግርግር  እንደከዚህ ቀደሙ ባለመኖሩ፤ ለአፍታም ቢሆን  የመዲናይቱ ጎዳናዎች በፀጥታ ድባብ  ተዋጡ። አዲስ አበባ በአስፈሪ ዝምታ ተሞላች- ማክሰኞ፣ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓመተ ምህረት -ማለዳ።

በዕለቱ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ፤ የመጀመሪያው በህዝብ የተመረጡ ከንቲባ ከሆኑት ከዶክተር ብርሀኑ ነጋ ጋር፤ ከረፋዱ 4 ሰዓት ላይ ለቃለ ምልልስ  የተያዘ  ቀጠሮ አለኝ።

ችሎት ከሚገኘው ቤቴ  ተነስቼና በናይጀሪያ ኤምባሲ አቆራርጬ ፤ ከሰሜን ሆቴል እና ከዮሀንስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ፤ በተለምዶ ዳትሰን ሰፈር ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ወዳለው ቢሮዬ  በእግሬ ስጓዝ  እንዳስተዋልኩት፤  ራቅ ብሎ  በሚሰማ  ዋይታ መሰል ጫጫታ  መሀል ፤ አልፎ አልፎ  ፤ እዚህም እዚያም  እንደበቆሎ እሸት የሚንጣጡ የጥይት ድምፆች ያስተጋባሉ።   ቀደም ሲል ፤ ማለትም ሰኔ 1 ቀን  ሙሉ ሌሊት ፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚወጣው  የተማሪዎች የነፃነት ዝማሬ፤ ወደሰፈራችን እያስገመገመ  በመዝለቅ፤ በብዙዎች ልብ ላይ የነፃነት ጥማትን አቀጣጥሏል።በዛሬዋ እለት ያ ዝማሬ እያስተጋባ ያለው ግን፤ ከዩኒቨርሲቲው ግቢ ብቻ አይደለም-  አዲስ አበባ  ጫፍ እስከ ጫፍ የተጫጫናትን ጥቁር ደመና  ፤ በነፃነት ዝማሬ  ለመግፈፍ ፤ ስልጡን  በሆነ እና ህግን በጠበቀ መንገድ፤  ገና በማለዳው ሰላማዊ  ድምፁዋን ማሰማት ጀምራለች።"**ድምፃችን ይከበር! ጠመንጃ ይብቃ! ምርጫችን ቅንጅት ነው! ቅንጅት ፍቅር ነው!**' የሚሉት  ፤በየቦታው ከሚያስተጋቡት   ድምፆች  ጥቂቶቹ ናቸው።

ልክ ከጧቱ 2 ሰዓት ላይ  ቢሮዬ ደርሸ  አንዳንድ   የያዝኳቸውን ስራዎች  በፍጥነት ካጠናቀቅኩ በሁዋላ ፤ የቃለ ምልልሱ ቀጠሮ ሰዓቱ እስኪደርስ ድረስ ፤ ከተለያዩ የመዲናይቱ ስፍራዎችና ከበርካታ ከተሞች  ያለ አንዳች ፋታ ወደ ቢሮአችን እየጎረፉ ያሉትን የስልክ ጥሪዎች እና የፋክስ መልዕክቶች  ከባልደረቦቼ ጋር በመሆን መቀበል ጀመርኩ።አብዛኛቹ ጥሪዎችና መልእክቶች ይዘታቸው አንድ ነበር- "ፌዴራል ፖሊሶች በእዚህ አካባቢ ተማሪዎችን ስለመቱ ሪፖርተር አሰማርታችሁ  ለህትመት አብቁት፣ የሰፈራችን ልጆች በታጣቂዎች ስለተከበቡ ጋዜጠኛ ልካችሁ ጉዳዩን ዘግቡልን፣በዚህ ከተማ እንዲህ ፣ በዚህኛው ደግሞ እንዲያ ስለሆነ  የጋዜጠኛ ቡድን ላኩልን" የሚሉ የተማፅኖ ጥያቄዎች።

ምን እናድርግ?   ከህዝብ  ወደ ዝግጅት ክፍላችን እየጎረፈ ያለው፤ የጋዜጠኞች ቡድን ስምሪት ጥያቄ ብዛት፤ እንኳን በነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ፤በነ ቢ.ቢ.ሲ እና በነ ሲ. ኤን. ኤን የሰው ሀይል  የሚሸፈን አይደለም።በአጭር ጊዜ በህዝብ ልብ ውስጥ የገባውና  ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘው  ነፃነት ጋዜጣ ፤በዛሬዋ ዕለት ህዝብ የማገልገል ሙያዊ ሀላፊነቱን እንዴት ይወጣ? አላባራ ላለው የህዝብ  ጥያቄ ምን ተግባራዊ ምላሽ ይስጥ?

ከቢሮ ባልደረቦቼ ጋር በዚህ ዙሪያ ስንነጋገር ነበር  ፤በድንገት የአዲስ አበባ ሰማይ በየአቅጣጫው  ድምፁ በሚያሸብር መሳሪያ  መታረስ የጀመረው።

ወቅቱ፤ የአፍሪካ ገዥዎች  አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ የተቀመጡበት ከመሆኑ አንፃር፤ ፋታ ለነሳው  ለዜጎች ሰላማዊ ተቃውሞ ፤ገዥው መንግስት  የሀይል እርምጃ ለመውሰድ፤ ቢያንስ ያንን ቀን ይመርጣል ብሎ ለመገመት፤   ህሊና ላለው ዜጋ ሁሉ በጣም ይከብዳል።ሁኔታውን ለመመልከት ወደ ውጭ ስንወጣ  ግን ፤ እየሆነ ያለው ፤ ከብዙዎቻችን ግምት ውጭ የሆነ ነገር ነበር።

አዎ! እሪታና ኡኡታው  ተደበላልቋል። ወላጆች ነጠላቸውን እያወዛወዙና “ዋይ ዋይ”እያሉ  ለጨዋታም ሆነ ለትምህርት ፤ከቤት ወጣ ያሉ ልጆቻቸውን  ከያሉበት ለማምጣት በባዶ እግራቸው ላይ ታች ሲሮጡ፤ የሩምታው ደምፅ የቀረበ ሲመስላቸው  በየሰው ቤት ሲጠለሉ፤   አንዳንዱ ወደ ላይ ፤ገሚሱ ወደ ታች፤ ሌላው ወደ ቀኝ ፤የተቀረው ወደ ግራ ሲርመሰመስ፤ አገር አማን ብለው  መኪናቸውን ይዘው የወጡ ጥቂት  ሰዎች  በየቦታው እያቆሙ በየደረሱበት ሲከትሙ፤ በአንፃሩ ጎዳናዎች በአልሞ ተኳሾች  ሲሞሉ.......ወዘተ  በህልም ዓለም የሚታይ  ትዕይንት እንጅ ፤ ገሀድ ክስተት አይመስልም ።መኖሪያ ቤቶችን፣ሱቆችንና ቡና ቤቶችን ጨምሮ  ማናቸውም ህዝባዊና መንግስታዊ ተቋማት ፤ከመቅፅበት ዳር እስከ ዳር ተዘጉ።አዲስ አበባ ያለማቋረጥ በጥይት መናጧን ቀጠለች። ከአፍሪካ መዲናነት በደቂቃዎች ውስጥ  ወደታላቅ የጦርነት አውድማነት ተቀየረች። አጠቃላይ የከተማዋ ምፅዓት ቀን የደረሰ መሰለ። ከየካቲት 12ቱ በከፋ ሁኔታ  አዲስ አበባ መቀጥቀጥ ጀመረች።አዎ!የጥቅምት 22ቱን በትር ከየካቲት 12ቱ የከፋ የሚያደርገው፤ የዚህች ቀን አዝማቾች-  ግራዚያኒ በጨፈጨፉቸው ሰማዕታት ሐውልት ስር ፤በየዓመቱ ጉንጉን አበባ የሚያስቀምጡ በመሆናቸው ነው።አዎ! ሰዎቻችን በየዓመቱ የካቲት 12 ቀን ስድስት ኪሎ በሚገኘው የሰማዕታት ሐውልት ስር አበባ ሲያስቀምጡ ፤ከመታሰቢያነቱ ባሻገር ፤እነሱ የዚያን ዓይነት ጭፍጨፋ ላለመፈፀም በልባቸው ቃል እየገቡ የሚፈፅሙት ትዕይንት ይመስለኝ ነበር።ግምቴ ትልቅ ስህተት ነበር።

የተኩስ ሩምታው  ፍጥነቱንና ድምፀቱን ይበልጥ በመጨመር የመዲናዋን ሰማይ ማረሱን ቀጠለ።በተለይ የቢሮዬ የቅርብ አዋሳኝ የሆነችው መርካቶ፤ ስንት ሜካናይዝድ  እንደሆነ ባልተገለፀ የአግዓዚ ጦር፤ ግቢ ነፍስ -ውጭ ነፍስ ውስጥ ገብታለች። ይህን ሁናቴ ካስተዋልኩ በሁዋላ ነበር ተመልሼ ወደ ቢሮዬ በመግባት  አንድ ስልክ የደወለወኩት

**ወዴት?**

***ወደ ቅንጅት ዋና ፅህፈት ቤት***

**ለምን?**

***ከዶክተር ብርሀኑ ጋር የያዝኩት ቀጠሮ በ እርሳቸው በኩል እንደተጠበቀ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ።***

ለረዥም  ጊዜ ተይዟል የሚል ድምፅ ያሰማ የነበረው ስልክ እንደምንም መለቀቁን ተከትሎ ፤አንድ ድምፅ “ሀሎ”  ሲል በጆሮዬ  አስተጋባ።የዶክተር ብርሀኑ ለመሆኑ አልተጠራጠርኩም። አዎ! በትክክልም እርሳቸው ነበሩ። ቀደም ሲል ለቃለ ምልልስ ያዘጋጀሁዋቸው ጥያቄዎች ፤በተፈጠረው ያልተጠበቀ ሁኔታ መቀየር  እንዳለባቸው  ወሰኛለሁ።እናም ከሰላምታው በማስከተል የቃለ- ምልልስ ቀጠሮ እንዳለን አስታወስኳቸው።” አገር እየጠፋ ምን  ዓይነት ቃለምልልስ ይደረጋል? “ አሉኝ። እንድንነጋገር የፈለግኩት በዚሁ ጉዳይ እንደሆነ ገለፅኩላቸው። ትራንስፖርት በሌለበትና እንደዚያ አስፈሪ በሆነበት ሁኔታ መምጣት የምችል ከሆነ፤ እርሳቸው ቃለ -ምልልሱን ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ገለፁልኝ።

ቀጣዩ ተግባር  በእንደዚያ ዓይነት ሁናቴ ፤ እንዴት ከዳትሰን ሰፈር ቦሌ ድረስ መሔድ ይቻላል? የሚለው ነበር። በአጭሩ ፤ መቅረፀ- ድምፄን ና ካሜራዬን በመያዝ ፤ አልፎ አልፎ ከሚታዩ  አንዳንድ ሰዎች በስተቀር፤ ከሲቪሉ ህብረተሰብ ጭር ያለውንና - በወታደራዊ ተሽከርካሪዋች የተሞላውን አስፋልት  በማቆራረጥ፤ እስከ አራት ኪሎ ድረስ ያለውን መንገድ በእግር አጠናቀቅኩ። በዚህ  ጦርነት መሰል የመጀመሪያ ቀን ፤ከአራት ኪሎ  እስከ ቦሌ ያለው አካባቢ ትንሽ  ቀለል ያለ ስለሚመስል ፤ በየቦታው በቁጥር የሚጠቀሱ ሁለትና ሶስት ላዳ ታክሲዎች ውር ውር ሲሉ ይስተዋላሉ። ሆኖም፤ እያንዳንዳቸው  አካባቢያቸውን  አልፈው  በመቶ እርምጃዎች ከሚቆጠር  ርቀት  በላይ ለመሄድ ስለማይደፍሩ፤ ከአራት ኪሎ -ቦሌ አስከሚገኘው ቅንጅት ፅህፈት ቤት ድረስ ላለችው  ከአምስት ፌርማታ ለማትበልጥ መንገድ፤ በየቦታው አራት ታክሱዎችን እያቆራረጡ መያዝ ግድ ነበር።

አሁን 5 ሰዓት ከ 12 ደቂቃ ሆኗል-ከረፋዱ።ከተማዋን እየናጠ ያለው ተኩስ ፤ቅንጅት ፀህፈት ቤት አካባቢም ያስተጋባል።ከታክሲ ወርጀ ወደ ቢሮው ሳመራ፤ ሲቪል ልብስ የለበሱ  አምስት ሰዎች  የትኩረት ዕይታቸውን ወደ ፅህፈት ቤቱ በማድረግ፤ ከዋናው በር መግቢያ ፈንጠር ብለው ቆመዋል። የደህንነት ሀይሎች መሆናቸውን አልተጠራጠርኩም።ወትሮም እዚያው ስፍራ ላይ እየቆሙ ቅንጅት ፅህፈት ቤት የሚገባውንና የሚወጣውን እንደሚከታተሉ አውቃለሁ።

ወደ ውስጥ ስዘልቅ በዚያ አስፈሪ ሁኔታ፤ ፊታቸው  ላይ ወገናዊ ሀዘንና ቁጣ  የተቀላቀለ ስሜት የሚታይባቸው፤ ሁለት ሰዎች በየቢሮአቸው ተቀምጠው  ተግባራቸውን ያከናውናሉ።

“ **ለምን** “ብለው ከማይጠይቁ ና ” **አድርጉ** “የተባሉትን ከማድረግ ከማይመለሱ የደህንነት ሀይሎች ጋር በመስኮት፤ ፊት ለፊት ዐይን ለዐይን እየተያዩ ፤ ያውም በእንደዚያ ዐይነቱ ወቅት፤ ድርጅታዊ ስራን እንዴት መስራት ይቻላል? ሁለቱ ሰዎች ግን ጥቅምት 22 ቀን የአዲስ አበበ ሰማይ በጥይት እየተናጠ ባለበት፣”**ተኩስ**” የሚል ትዕዛዝ አኮብኩበው በሚጠባበቁ ደህንነቶች በተከበቡበት እና በደጋፊዎችቻቸው ላይ የተከፈተው ጦርነት በነሱ ህይወት ላይ ምን ሊያመጣ እንደሚችል መገመት በሚያስቸግርበት በዚያ ቀውጢ ጊዜ ፤ቢሮአቸው ውስጥ ገብተው ይጣደፉ ነበር። ዶክተር ብርሀኑ ነጋና ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ።ከሁለቱም ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በሁዋላ ፤ ከዶክተር ብርሀኑ ጋር ወደ ቃለ ምልልሱ ገባን።

አጠቃላይ የቃለ ምልልሱ ጥያቄ ጭብጥ፤” ***ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ ይመስላሉ፤ አገር እየጠፋ ነው። እየሆነ ባለው ነገር ያላችሁ መረጃ ምንድነው? ይህ ቀውስ እንዴት ተፈጠረ? እንዲቆምስ በናንተ በኩል ምን ጥረት እያደረጋችሁ ነው?***”የሚል ነበር።

ከንቲባ ዶክተር ብርሀኑም፤ በዕለቱ እያከናወኑት ያለው ተግባር ከዚሁ ጋር የተያያዘ እንደሆነ፣ወደተለያዩ ስፍራዎች ስልክ በመደወልና አባሎቻቸውን በማሰማራት በርካታ መረጃዎችን እንዳሰባሰቡ፣ ሁሉም መረጃዎች -በየቦታዎች የተፈጠሩትን ግጭቶች ሆነ ብለው ታጣቂዎች እንደፈፀሚቸው እንደሚያመለክቱ፤ገዥው ፓርቲ ከተለያዩ ጠባብ የፖለቲካ ጥቅም ስሌቶች በመነሳት ሆነ ብሎ እንዲፈጠር ያደረገው ቀውስ ስለሆነ፤ ይህን ማስቆሙ ከቅንጅት አቅም በላይ እንደሆነ፤ የጨዋታውን ካርድ የያዘው ገዥው ፓርቲ በአስቸኳይ የተፈጠረውን ቀውስ ያስቆም ዘንድ ለማሳሰብ በተደጋጋሚ ለመንግስት አካላት ያደረጉት የስልክ ጥሪ፤ ምላሽ ማጣቱን፤ ከእንግዲህ የመጣውን ነገር ከህዝባቸው ጋር በመሆን ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን በተብራራ መልኩ ገለፁልኝ።

ቃለ ምልልሱ ተፈፀመ። ምስጋና ካቀረብኩ በሁዋላ ሁለቱንም ተሰናብቼ ቢሮውን ለመልቀቅ ስንደረደር “ ደረጀ” በማለት ጠሩኝ=ዶክተር ብርሀኑ።”አቤት “አልኩኝ ወደ ሁዋላ በመመለስ። “ነፃነት ጋዜጣ ሐሙስ ነው የሚወጣው አይደል?” በማለት ጠየቁኝ። ራሴን በአዎንታ ነቀነቅኩ።” በል ጋዜጣው እንደወጣ ያለሁበት ስፍራ እንድታመጣልኝ”አሉኝ- ሀዘንና ቁጭት በተቀላቀለበት ስሜት።አባባላቸው ሊገባኝ ስላልቻለ “ የሚሉት አልገባኝም ዶክተር ብርሀኑ” አልኳቸው። **“ ይህን ጋዜጣ እስር ቤት ሆኘ ነው የማነበው”** አሉኝ። እኔም “አይመስለኝም፤ ኢህአዴጎች ይህን የሚያደርጉት አይመስለኝም፤ ምን ስላደረጋችሁ ያስሯችሁዋል?” ስል ጥያቄ አዘል አስተያየቴን ሰነዘርኩ- እርግጠኛ በመሆን የሰጠሁት አስተያዬት ነበር። እርሳቸውም :-” ምንም ስላደረግን ሳይሆን፤ ኢህአዴግ ማሰር ስለፈለገ ነው የሚያስረን፤ ብቻ ጋዜጣውን እንድታመጣልኝ... በል ደህና ዋል... ስትሄድ እነዚህ ውጭ ጋር ያሉት ደህንነቶች እንዳይጋጩህ ተጠንቀቅ፤ ቢናገሩህም እንዳትመልስላቸው ... ቻዎ” አሉኝና -ተሰነባበትን።

በመጣሁበት ሁኔታ ቢሮዬ ተመልሸ ስደርስ ከቀኑ 7 ሰዓት ተኩል ሆኗል። ከመርካቶ የሚያጓራውን የጥይት ድምፅ እንደምንም ሳይቆጥሩ ፤ሁሉም ባልደረቦቼ ከሙቼውም ጊዜ በላይ ለስራ ሲራወጡ በመድረሴ በጋዜጠኝነቴ ኮራሁ።ከየአቅጣጫው የሚጎርፈው የስልክ ጥሪና መረጃ፤ አሁንም አላቋረጠም........ ቃለምልልሱን ከመቅረፀ ድምፄ ገልብጨ በመስራት ላይ እያለሁ ፤አንድ- የቃለ ምልልሱን ርዕስ ሙሉ በሙሉ የቀየረ የስልክ መረጃ ተቀበልን። ኢንጂነር ሀይሉ እና ዶክተር ብርሀኑ በታጣቂዎች ተይዘው፤ ማዕከላዊ ታሰሩ የሚል መረጃ። ቢሮው ለአፍታ በፀጥታ ተሞላ።ከአፍታ ዝምታ በሁዋላ፤ወደ ቅንጅት ፅህፈት ቤት ስልክ በመደወል ፤በዚያ ሰዐት በፅህፈት ቤቱ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ከነበሩት ከወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳ ፤ የመረጃውን ዕውነተኛነት አረጋገጥን።

የዶክተር ብርሀኑ ቃለምልልስ “ **ይህን ጋዜጣ እስር ቤት ሆኜ ነው የማነበው” በሚል ርዕስ ተሰራ**።”አደራ” እንዳሉኝም ጋዜጣው ሐሙስ ዕለት ለንባብ ሲበቃ ማዕከላዊ ልወስድላቸው ለራሴ ቃል ገባሁ።ይህን ሁሉ ገልጩ ለባልደረቦቼ ስነግራቸው- ሁሉም በጥልቅ አዘኑ።

ሆኖም፤ በማግስቱ ረቡዕ በኢትኦጵ ጋዜጣ ላይ የተወሰደው ህገወጥ እርምጃ፤ የኢትዮጵያ ግል ፕሬሶችን መፃኢ የጨለማ ጊዜ ያመላከተ ነበር። የተወዳጁ ኢትኦጵ ጋዜጣ አሳታሚና ባለቤት ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና፤ ለ88 ሸህ ጋዜጣ ብዙ ሸህ ብር ከፍሎ ጋዜጣው እየታተመ ሳለ፤ ገንዘቡ ሳይመለስለት ህትመቱ እንዲቆም መደረጉን ለቪ. ኦ. ኤ ቃለ ምልልስ ሲሰጥ ሰማሁ። ብዙም ሳልቆይ ቢሯችን በስድስትት ታጣቂዎች መከበቡ በስልክ ተነገረኝ።ረቡዕ ምሽት በተላለፈው በምስል በተደገፈ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዜና፤ የሐዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደና ምክትሉ ፈለቀ ጥበቡ ከቅንጅት አመራሮች ጋር ማዕከላዊ ገብተው ታዩ።አሁን ቀጣዮቹ ታሳሪዎች እነማን እንደሆኑ መገመት አልቸገረኝም።አዎ! ከዜናው ቀጥሎ “ ህገ መንግስቱን በሀይል በመናድ አደገኛ ወንጀል የሚፈለጉ” በሚል ርዕስ ወደ 30 የሚጠጉ ተፈላጊዎች ስም ተዘረዘረ። ከነዚህ ተፈላጊዎች ውስጥ ፤አንዱ ይህ ጋዜጠኛ ሆነ- ጋዜጠኛ ደረጀ ሀብተወልድ።

ከሶስት ቀን በሁዋላ ከአምስት ሌሎች ተፈላጊ ጓደኞቼና የሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን ማዕከላዊ በመሄድ እጃችንን ሰጠን።እስር ቤት በገባን በሶስተኛው ቀን ፤ በሌሎቹ እስረኞች እንደተደረገው ሁሉ በአራት ፖሊሶች ታጅቤ መኖሪያ ቤቴን ለማስፈተሽ ተወሰድኩ።ቀደም ሲል ለተመሳሳይ ፍተሻ ወደ ቢሮአችን ተወስጀ፤ ሰነዶችን፣ ወረቀቶችን፣ ኮምፒውተሮችንና የፋክስ ማሽኖችን ጨምሮ በቢሮአችን የነበሩ ዕቃዎች በሙሉ በፖሊሶች መወሰዳቸውን ተመልክቻለሁ።በዚህ ወቅት ፤የዶክተር ብርሀኑን ቃለምልልስ በእጅ ፅሁፍ የፃፍኩበት ወረቀት፤ አብሮ ከቢሮ ተወስዷል።

ቤቴ ውስጥ መደርደሪያዬ ጫፍ ላይ ለስራ ለይቼ ያስቀመጥኳት የቃለ ምልልሷ ካሴት ደግሞ ፤ከዛሬው ፍተሻ የምትተርፍ አልመሰለኝም። አዎ! የፈራሁት አልቀረም፤ ፈታሾቹ የመጀመሪያ ታርጌታቸው መፅሀፍና ከሴት ነበርና የቃለ ምልልሷም ካሴት እያየሁዋት አብራ ተጫነች።አብራ ታሰረች። በዚያ ሁኔታ ውስጥ ፤ዶክተር ብርሀኑ “ይህን ጋዜጣ እስር ቤት ሆኘ ነው የማነበው” ያሉኝ ትዝ አለኝ። ትክክል ነበሩ። ከእርሳቸው ጋር ፣ ጋዜጠኛውም፣ ቃልልሱም አብረው መታሰራቸውን ሳይ ደግሞ ፤በልቤ ፈገግ አልኩ። ሶስተሰችንም ለሁለት ዓመት ቃሊቲ ታስረን ከረምን- ዶክተር ብርሀኑ፣ እኔና በእኔ ትውስታ ውስጥ የነበረው የሁለታችን ቃለ-ምልልስ - ያውም በአንድ ግቢ ውስጥ። እነሆ ሶስታችንም አብረን ተፈታን።

**“ ኤፍታህ!”**

ሁላችንንም፤ እግዚአብሔር ይፍታን፣ አሜን።